# የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ፈተና

የፈለግነው ስለሆን የፈለጉትን የሆኑ ሰዎችን ስኬታማነት እንደምናጠና ሁሉ ፤ ያልፈለገነውን ባለመሆን ደግሞ የፈለጉትን መሆን ያቃታቸውን ሰዎች ብናጠና እራሳችንን ከሽንፈት እንጠብቃለን። ሰዎች መሆን ያቃታቸው ፣ ከሁሉም በላይ የባህሪ ድክመት ተጠቂ በመሆናቸው ነው። በሽታ የሰውን አካል ይጎዳል፤ ያዳክማል። ህመምተኛው ህመሙን በጊዜ ካልታከመው የከፋ አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል። የባህሪ ድክመት የመንፈስና የስነልቦና በሽታ ነው። የአንድ ሰው ባህሪ በበሽታ ሲጠቃ የተመኘውን መሆን ትቶ ያልተመኘውን ይሆናል።

ባህሪን ከሚያጠቁ በሽታዎች አንዱ ወላዋይነት ወይም ባላማ አለመጽናት ነው። ወላዋዋይነት ብዙ ሰዎችን ያጠቃ በሽታ ነው። ወላዋይ ሰው የሚደርስበት ውጤት አለመሆንን ነው። ለምሳሌ ስፖርተኞችን እንመልከት።

በውድድራቸው የሚወለውሉ ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ የማሸነፋቸው ነገር አጠራጣሪ ይሆናል። መሆን ወይም አለመሆን በራሱ አንድ ውድድር ነውና። አንድ ሰው የፈለገውን ለመሆን በሚጥርበት ጊዜ ዋናው ተወዳዳሪው አለመሆን ነው። ወላዋይነት ደግሞ አለመሆን እንዲያሸንፍ ክፍተት ይሰጠዋል። ወላዋይነት የአዕምሯችን ተሳትፎ ውስን ያደርገዋል።

አእምሯዋችንን ከመኪና ጋር ማወዳደር እንችላለን። አእምሯችን መኪና ቢሆን ከመሪው በኋላ የምናገኘው ሹፌር ወይም እያንዳንዳችን ነን። መኪናው ብልሽት እስከ ሌለው ድረስ የፈለግንበት ቦታ ለመድረስ የሹፌሩ ተሳትፎ ወሳኝ ነው። መኪናውን ይዘን ከመነሳታችን በፊት ወዴት እንፈምንሄድ አውቀን በእርግጠኝነት ካልተነሳን  መኪናው ውስጥ ገብተን የምናመነታ ከሆነ የፈለግነው ቦታ የመድረሱ ነገር ሊስተጓጎል ይችላል።

በእርግጥ ወላዋይነት የሚጠቃቸው ሰዎች ለድክመታቸው የሚያቀርቡት ምክንያት አለ። ይሁን እንጂ ምክንያቱ የፈለጉትን ትተው  ያለፈለጉትን ለመሆን በቂ ምክንያት አልነበረም። ሌሎች ብዙ ሰዎች የፈለጉትን መሆን የቻሉት፣ እነዚህን እነሱ ምክንያቶች ብለው የሚያቀርቧቸውን ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ተመሳሳይ ገጠመኞች አልፈው ነው።

ወላዋዮች ግን ምክንያት በመፍጠር ወላዋይነታቸውን ያጠናከራሉ። ስለዚህ ለውጥ ማምጣት ያቅታቸዋል። የፈለጉትን ለመሆን ከብዙ ሰዎች ለመውጣት የሚያስፈራ ተራራ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ከደረስንበት ደረጃ ዝቅ ሳንል ደረጃችንን ጠብቀን መኖር በራሱ ትግል ነው። ብዙ ፈተናንና ትግል ረባዳ ቦታ ይመርጣሉ፤ የፈለጉትን ለመሆን የሚጥሩ ሰዎች ግን በፍጹም ረባዳ ቦታን አይቀበሉም። እንዳጋጣሚ ሆኖ ራሳቸውን እንዲህ ዓይነት ቦታ ቢያገኙትም እዚህ ለመግባታቸው ምክንያት ሰጥተው ተደላድለው አይቀመጡም። ወላዋይ ሰዎች ግን በሕይወታቸውም የትም አይደርሱም።

**ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጡ።**

1. በምንባቡ መሰረት ራሳችንን ከወላዋነት ልንከላከል የምንችለው እንዴት ነው?

   ሀ. የፈለጉትን የሆኑና ያልፈለጉትን የሆኑ ሰዎችን ሕይወት በማጤን፣

   ለ. የፈለጉትን መሆን የቃታቸውን ሰዎች የሕይወት ዘይቤ በመከተል ፣

   ሐ. ያልፈለጉትን የሆኑ ሰዎችን የኑሮ ዘዴ ሳናወላውል በመከተል፣

   መ. የፈለጉትን የሆኑ ሰዎች የሚሰጡትን ምክንያት በማጤን

2. በምንባቡ መሠረት # የባህሪ ድክመት ተጠቂ ናቸው; የሚለው አገላለጽ ምንን ያመለክታል?

   ሀ. ከአመለካከት ጋር የተያያዘ ችግር

   ለ. ከአእምሮ ጋር የተያያዘ የሚፈጠር ፍርሐት

   ሐ. የስራ ልግመኝነት

   መ. የጉልበት ስንፍና

3. # ወላዋይነት ብዙ ሰዎችን ያጠቃ በሽታ ነው; የሚለው ሀሳብ በየትኛው ምሳሊያዊ አነጋገር ሊገላጽ ይችላል?

   ሀ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች

   ለ. አስር ጊዜ ለካ አንድ ጊዜ ቁረጥ

   ሐ. ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጧት

   መ. ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል

4. ከሚከተሉት መካከል የጹሁፉን አጠቃለይ መልእክት የሚጠቁመው የትኛው ነው?

   ሀ. የጸና አላማ ካለን የፈለግነውን መሆን እንችላለን

   ለ. የጸና ዓላማ እንዲኖረን ስፖርተኞችና ማየት እስተዋጽኦ አለው።

   ሐ. አእምሮ ከመኪና ጋር ማነጻጸር የጸና ዓላማ እንዲኖረን ይረዳል

   መ. የጸና ዓላማ እንዲኖረን ድክመታችንን ማመን ይኖርብናል።

5. በምንባቡ መሠረት # ረባዳ ቦታን; የማይቀበሉ የትኞቹ ናቸው?

   ሀ. ፈተናን የሚፈሩ      ሐ. በዓላማ የማይጸኑ

   ለ. ምክንያት የሚያበዙ      መ. የፈለጉትን ለመሆን የሚጥሩ

6. በምንባቡ ውስጥ #ቋሚ ትግል ነው; የተባለው ምንድን ነው?

   ሀ. ደረጃን ከፍ አድርጎ መኖር      ሐ. ዝቅ ብሎ መኖር

   ለ. ደረጃን ጠብቆ መኖር      መ. ዝቅና ከፍ ብሎ መኖር

7. ከላይ የቀረበውን ምንባብ በተመለከተ ጥልቅ ምርምር ማድረግ ቢፈለግ የበለጠ መረጃ ከየት ሊገኝ የችላል?

   ሀ. ከመገናኛ ብዙኃን      ሐ. ከባለሙያ

   ለ. ከመጻህፍት      መ. ሁሉም መልስ ናቸው

8. ስልምንባቡ የትኩረት አዝማሚያ ምን ማለት ያቻላል?

ሀ. የስኬታማ ሰዎችን ታሪክ የሚያነሳ ጹህፍ ነው

ለ. በጻህፊው ፍልስፋና ላይ የተመሰረተ ጹህፍ ነው

ሐ. በተጨባጭ መራጃ ላይ ያተኮረ ታሪክ ቀመስ ትረካ ነው

መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

**9.** የግጥም ባህሪ ያልሆነው ቱ ነው?

ሀ. ቁጥብ አይደለም ሐ. ዜማ አለው

ለ. ምት አለው መ. ምጣኔ አለው

10. ከሚከተሉት መካከል ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ ትርጉም የማይሰጠው

ሀ. ለጋ ለ. ዱካ ሐ. ሳለ መ. ገና

**11.** <u>**ውፍረት**</u> የተሰመረበት ቃል ጥገኛ ምዕላድ

ሀ. **-ኣት** ለ. **ረት** ሐ. ã**ት** መ.**-ት**

12. <u>ሰለጠነ</u> ይህ ግስ ወደ ቅጽል ሲቀየር

ሀ. ስልጡን ለ. ስልጣኔ ሐ. ስልጠና መ. ሁሉም

13. የዚህ ክፍል .................. (ጎበዘ) ተማሪ ዛሬ አልመጣም። በቅንፍ ውስጥ ያለው ወደ ቅጽል ተቀይሮ አረፍተ ነገሩን የሚሟላው........

ሀ. ጎበዘ ለ. ጉብዝናው ሐ. ጎበዝ መ. መ/የለም

14. <u>ማገጠ</u> የተሰመረበት ቃል ፍቺ ...........

ሀ. ባለገ ለ. ተበላሸ ሐ. ዋለወጌ ሆነ መ. ሀ እና ለ ሠ. ሁሉም

15. የአንድን ነገር ምስልና ገጽታ በቃላት አማካይነት ስሎ ለማቅረብ የሚሞክር.............

ሀ. ገላጭ ድርሰት ለ. ስዕላዊ ድርሰት ሐ. ድርሰት መ. ተራኪ ድርሰት

16. ከሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ ጠብቆና ላልጦ ሲነበብ ትርጉም የማሰጠው የቱ ነው?

ሀ. ለጋ ለ. ዱካ ሐ. ሳለ መ. አለ

17. <u>ውፍረት</u> የተሰመረበት ቃል ጥገኛ ምእላዱ

ሀ. **-ኣት** ለ. **ረት** ሐ. - ã**ት** **መ.-ት**

18. **ሰለጠነ** ይህ ግስ ወደ ቅጽል ሲቀየር

ሀ. ስልጡን ለ. ስልጣኔ ሐ. ስልጠና መ. ሁሉም

19. የዚህ ክፍል ...................... (ጎበዘ) ተማሪ ዛሬ አልመጣም። በቅንፍ ውስጥ ያለው ቃል ወደ ቅጽል ተቀይሮ ዓ.ነገሩን የሚያሟላው ............................ ነው።

ሀ. ጎበዘ ለ. ጉብዝናው ሐ. ጎበዝ መ. መ/የለም

20. ከሚከተሉት ውስጥ የክርክር አቀራረብ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. የመከራከሪያ ርዕስን ለአድማጬ ማቅረብ

ለ. ፍሬ ሃሳቦችን በቅደም ተከተል ማቅረብ

ሐ. የተቃዋሚ ሀሳብን በማዳመጥ ማስታወሻ መያዝ

መ. አለባበሳችንና ንጽህናችንን በስነ ስርዓት ማሟላት

21. ከሁሉም ይለያል ያለቃችን ሆድ፣

ሰው ለቁርሱ ሲሮጥ መክሰስ ነው ሚወድ? የዚህ ግጥም ህብረ ቃል ................ ነው።

ሀ. ሆድ ለ. መክሰስ ሐ. ለቁርስ ሲሮጥ መ. ያለቃችን ሆድ

22. ለምን መጣህ ይህ አ.ነገር ................... ነው።

ሀ. ትዕዛዛዊ ለ. አሉታዊ ሐ. ጥያቂዊ መ. ሀ እና ሐ

23. የአገሬ ገበሬ ቅኔውን ሲቀኘው

ውሎ አድሮ ቆጥሮ ነው፣

ቶሎ ቶሎ መዝረፍ እንደተገኘ ነው። የዚህ ግጥም ህብረቃሉ ................ነው።

ሀ. ተገኘ ለ. መዝረፍ ሐ. ቶሎ ቶሎ መዝረፍ መ. እንደተገኘ

24. ጦርነት አልወድም............... በሀገሬ አልደራደርም።ይሀ አ.ነገር ሊያይዝ የሚችለው

ሀ. ስለዚህ ለ. ይሁን እንጅ ሐ. በመሆኑ መ. ባንጻሩ

25. ህቡእ ለተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፈቺ ሊሆን የሚችለው፡

ሀ. ድብቅ ለ. ስውር ሐ. ሚስጥራዊ መ. ሁሉም

በ **ሀ** ስር የተዘረዘሩትን ከተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር በ **ለ** ስር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ

| **ሀ** | **ለ** |
|---|---|
| 26. ሳንቃ | ሀ. ብብት |
| 27. ጉልላት | ለ. ከሸክላ የሚሰራ የውሃ መያዣ |
| 28. ጉስጉሻ | ሐ. በር |
| 29. ጉያ | መ. የሊጥ ማቡኪያ |
| 30. ሙሃቻ | ሠ. ትንሽ የእህል ማስቀመጫ |
| 31. ለምድ | ረ. ከቤተክርስቲያን (ከሳር) ቤት ጫፍ ላይ የሚገኝ |
| 32. ቶፋ | ሰ. ከፍየል ቆዳ የሚሰራ የእህል መያዣ |
| 33. ስልቻ | ሸ. ከቆዳ የሚሰራ ልብስ |

**የሚከተሉትን ስለ ግጥም የሚያወሱ ጥያቄዎች ከትርጉማቸው ጋር አዛምዱ**

| | |
|---|---|
| 34. ምጣኔ | ሀ. በጥቂት ቃላት ብዙ ማለት የሚችል |
| 35. ምት | ለ. በየሐረጉ ከ1-4 ቀለም የሚይዝ |
| 36. ቁጥብነት | ሐ. በሐረግ 6 ቀለማትን የሚይዝ |
| 37. ዜማ | መ. የተስተካከለና የተከረከመ ምት ሲኖር የሚኖር ነው |
| 38. የወል | ሠ. የቀለማትን መጠን በሐረግ ውስጥ የምንመጥንበት |
| 39. ሰንጎ መገን | ረ. የሚመነጨው ከምጣኔ ነው |
| 40. ቡሄ በሉ | ሰ. በሐረግ ውስጥ 5 ቀለሞችን የሚይዝ |

ትምህርት በቤቱ

@Timehirtbebet